# በተፈጥሮ ሀብትሽ ነግሷል ድህነትሽ

ከአብርሃም በየነ

የባዕድ ጆሮ ጠቢ - ሰባቂ ምንደኛ፣

መሪሽ እንደራሴው - ምሁርሽ ቅጥረኛ፤

የሶስተኛው ዓለም - በተለይ አፍሪቃ፣

የድንቁርናን ጌጥ - የድህነት ዶቃ፣

የግፍ ቀንበር ገዝቶ - በሀብትሽ ሰቆቃ፤

ዩራኒየም ኮባልት - አልማዝና ብሩ፣

የወርቅሽ ማዕድን - ዘይተሽ አፈሩ፣

የውሃ ፍሳሽ ሀብትሽ - ወንዝሽ ሸንተረሩ፣

ወይ አቀማመጥሽ - ከነመልክዓ ምድሩ፣

ወይ የህዝብሽ ብዛት- ፈጣን ዕድገት ቁጥሩ፤

እያለሽ የሌለሽ - ድሃ ሀብት አፍላቂ፣

ርሃብ የፈታው - የሞት ስንቅ ሰናቂ፣

ሀብትሽ ነው ያረገሽ - በራስሽ አላቂ።

ሀብትሽ በእጅሽ ይሁን - መመዝበርሽ ይብቃ፣

ህዝብሽ ከምኝታው - ተቀስቅሶ ይንቃ፤

ከአልጀሪያ እስከ ጁባ - ከቻድ እስከ አንጎላ፣

ከኒገር ሞዛምቢክ - አቢሲኒያ አዶላ፣

አመፅ ነው መፍትሄው - ጥቁሩ ደም ሲቀላ፤

ለዓለም ይሁን ይፋ - በነጋሪት አዋጅ፣

ቀንበርሽ ይሰበር - ምድሩም በደም ይዋጅ።

ግንቦት 2002